ጸሎት

እግዚአብሔር ምሕረቱን ያብዛልን:: በረከቱን ያድለን:: ፊቱን ያብራልን:: የምሕረት ዐይኖቹም ዘወትር ወደ እኛ የሚመለከቱ ይሁኑ:: ርኅራኄውን ያድለን:: ንጽሕት በምትሆን በእግዚአብሔር ወልድ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም ጸሎትና ምልጃ፤ በመላእክት፣ በሐዋርያት፣ በነቢያት፣ በሰማዕታት፣ በጻድሳት፣ በባሕታውያን፣ በቅዱሳን ሁሉ ጸሎት:: በሁሉም ጊዜ ሰላሙን እንዲያድለን በሚጸልዩልን የቅዱሳን በረከት፣ የቅድስት ድንግል ማርያም በረከት ቅዱስ የሆነ በረከታቸው፣ ጸሎታቸውና አማላጅነታቸው ሁሉ ከእኛ ጋር ይሁን አሜን::

Scanned by CamScanner

Project information

ነፍሴ የመደደችህ

የውኃውን መልክ መለወጥ እንደሚቻላት በጣም ጥቃቅን እንኳን የምንለው ኃጢአት ውጤቱ አውዳሚ ነው። እግዚአብሔርን የምትወደው ከሆነ ዓለም በዐይንህ ፊት እያነሰ ይመጣል። «ከንቱና ነፋስንም እንደመከተል» ይሆንብሃል /መክ.፩፥፲፬/ ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው «አዎን በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ፥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ፣ ስለጌታዬ ዕውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን ቆጥሬአለሁ» ትላለህ /ፊል.፫፥፰/ ።

እግዚአብሔርን ለወደዱ ቅዱሳን ዓለሙ በሙሉ ረብህ የሌለው ነገር ነበር። ቅዱስ አውግስጢኖስ እንዲህ ይላል። «ማንንም ሳልፈራ ዓለምን በተከተልኩ ጊዜ፥ በዓለም ቁንጮ ላይ ነበርሁ።» ዓለምን ስትወድ በአስተሳሰብህ ሁሉን ነገር ወደ አንተ ማምጣት እንደማይቻልህ፣ በዓለም ጫፍ ላይ እንደቆምክ ታስባለህ። ከዓለማዊ ነገር መላቀቅም በቀላሉ ልታደርገው የሚቻልህ ነገር አድርገህ ታስባለህ። ወደሰማያትም በቀላሉ መውጣት የሚቻል ነገር አድርገህ ታስባለህ። ዓለምም ከእግርህ ሥር እንደሆነ ትገምታለህ። የእግዚአብሔር ፍቅር ሁሉንም ዓይነት አምሮት ከውስጥህ ፈንቅሎ ያወጣልሃል። በዓለማዊ ጥበብ ግን ዓለምን መውደድ እንጂ፣ መጥላት አይቻልም። የእግዚአብሔር ስም ባሬም ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን።

Reported to(Project Mgt. Consulta
Name
Signature
Date
Habtamu.M
08/05/2021
Date
ature

Scanned by CamScanner

ፍላጎቶች የሉምና። በዚያን ጊዜ ምን ማለት ይቻልሃል? ይቅርታ ሰማያት የእኔን ፍላጎት አያሟሉልኝም ወደ ምድር ልመለስ ማለት ይቻልሃልን? ወዳጄ ሆይ እርሱ እርባና ቢስና ተቀባይነት የሌለው ጥያቄ ነው።

ወደዘላለማዊነት ለሚደረገው ጉዞ ግንኙነትህን ከአሁኑ መጀመር ይኖርብሃል። በዚህ ዓለም ሳለህ ከዚያኛው ዓለም ጋር እንዴት ራስህን ማለማመድ እንዳለብህ መማር ይኖርብሃል። የሚመጣውን ዓለም ሕይወት ተለማመድ። ልትመራ የሚገባህ ለሚመጣው ዓለም ሕይወት የሚጠቅምህ መንፈሳዊ ልምምድ ነው። በምድር ላይ ሳለህ ከጌታ፣ ከመላእክት፣ ከቅዱሳኑም ጋር መኖር ይገባሃል። ዓለሙም ፍላጎቱም ሲያልፍ በዚህ ዓለምና በፍላጎቱም የተያዘ ሰው ዕጣ ምን ይሆናል? ምንስ ማድረግ ይቻለዋል?

ከጌታ ጋር ግንኙነት ይኑርህ። ምክንያቱም ግንኙነቱ የሚጀምረው በዚህ ዓለም ነውና። ነገር ግን ግንኙነቱ ፍጻሜ ያለው አይደለም። ለዓለም ያለህ ግንኙነትና ፍቅር በሞት በተጠራህ ጊዜ አንድ ቀን ፍጻሜውን ያገኛል። የቱንም ያህል ረጅም ጊዜ ብትኖር አንድ ቀን ይቆረጣል። ከጌታ፣ ከመላእክቱ፣ ከቅዱሳኑም ጋር ያለን ግንኙነት ግን ቀጣይነት ያለው ነው። በዚህ ምድር ላይ ሕይወትህን ይቋጫል ብለህ ፈጽመህ አታስብ። እንደዚያ ቢሆን ዕረፍት በሆነልህ ነበር፤ ነገር ግን አይደለም። የሚዘልቀው ነገር ቢኖር በዚህ ዓለም የሠራኸው መልካም ሥራ ሁሉ ነው። እግዚአብሔር የሕይወት ዘመን ጉዞህን ሁሉ ይመረምራል።

አንዲት ተራ ኃጢአት አጠቃላይ የሕይወት ዘመን ጉዞህን ልትገታው ትችላለች። እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው ፍቅሩ ጽኑና ጥብቅ ብቻ መሆን ያለበት ሳይሆን፤ ፍጹምና በሙሉ ልብ የሚደረግ መሆን አለበት። በውኃ ውስጥ ያለች አንዲት ጠብታ ቀለም

Scanned by CamScanner

ነፍሴ የመዱጂችህ

በተለይም በእግዚአብሔር ስም ስትጸም፣ ጸምህን ለእግዚአብሔር ክብር አድርገው። ደስታን በእግዚአብሔር ስም ተለማመድ። ስለ ስሙም ብለህ መከራን ተቀበል። በጌታ ሥም ንቃ፣ በስሙም ተኛ። እርሱን ለማገልገል የሚያስችል ዕረፍት ይሆንልሃል። ይህንን በተመለከተ የሐዋርያው ቃላት ምንኛ የተወደዱ ናቸው። «በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለን፣ ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን።» /ሮሜ ፲፬፥፰/። ልነግራችሁ የሚገባኝ አንድ ነገር አለ። በዚህ ዓለም አሁን የምትኖሩት ሕይወት ቀጥተኛና የተረጋጋ አይደለም። የመከራ ሕይወት ነው እንጂ። እግዚአብሔር ነጻ ፈቃዳችሁን ይፈትናል።

1.10. አንዲት ነጠላ ታጢአት ሕይወትህን በሙሉ ልታበላሽ ትችላለች

አንተን ልጠይቅ የምፈልገው አንድ ነጥብ አለ። ራስህንም እንድትጠይቅ ነው። በዘላለማዊነት የምትኖረው ከእግዚአብሔር ጋር ነው ወይስ ከሌላ? በዚህ ምድር ላይ በእግድነት ስትመላለስ ከእርሱ ጋር መሆን ካልተቻለህ፣ በሰማይ ከእርሱ ጋር መሆን እንደምን ይቻልሃል? በምድር ላይ ቢያንስ ለማማሽ ሰዓት ከጌታ ጋር መነጋገር ካልቻለህ ወደዘላለማዊ ሕይወት ስትጠራ ከእርሱ ጋር መነጋገር እንደምን ይቻልሃል? ከመላእክት ጋር ግንኙነት ከሌለህ ወዴት መሔድ ይቻልሃል? በምድር ላይ ከቅዱሳኑ ጋር አንድነት መፍጠር ካልተቻለህ በሰማይ ከእነርሱ ጋር አንድነት እንደምን ሊኖርህ ይችላል? የምትወደው ነገር ቁሳዊ ነገር ከሆነ እርሱንም ለማሚላት የምትድህ ከሆነ፣ ከዓለም ፍላጎትና ዝና ጋላ የምትሮጥ ከሆነ በሰማይ ስትሄድ ምን መሥራት ይቻልሃል? በዚያ የአንተ

Reported to(Project Mgt. Consu
Name
Signature
Date
Habtamu.M
08/05/2021
Signature
Date

በጋለ ስሜት፣ ራስን አሳልፎ በመስጠትና በታላቅ ጥንቃቄም የሚፈጽም ነው። በምትናገረው በማንኛውም ቃል እግዚአብሔርን በፊትህ አስቀድም። የጽድቅና የእውነት መንገድ ይሆንልሃል። ከጽድቅ መንገድ ራሱን የሚመልስ ወገን ራሱን በፈቃዱ ከእግዚአብሔር ለመለየት ፈቅዷል። «እኔ ሕይወትም መንገድም እውነትም ነኝ ብሏል/ ዮሐ ፲፬፥፮/።

ጽድቅና እውነት ከእግዚአብሔር ባሕርያት መካከል ናቸው። የማኅበራዊ ዕውቀት መገለጫ የሆነ ነገርን ወስዶ በእውነት የሚመላለስና በመለኮታዊ ፍቅር ተሞልቶ በፍቅር በሚመላለስ ወገን መካከል ከፍተኛ የሆነ ልዩነት አለ። በምትኖርበት ማኅበረሰብ ውስጥ ትክክለኛ ነገርን በራስህ ፍላጎት ተነሳስተህ ለመፈጸም በምታደርገው ፈቃድና ከእግዚአብሔር ላለመለየት ብለህ እውነትን የምትከተለው መንገድ ይለያል። ቅዱስ የሆነ ሰው ስሕተትን ሲሠራ ከእግዚአብሔር እንደተለየ ያስባል። «ጽድቅ ከዐመጻ ጋር ተካፋይነት የለውም። ብርሃንም ከጨለማ ጋር ኅብረት የለውም።» /፩ ቆሮ ፮፥፲፬/።

ሰውን ስታገለግል እግዚአብሔርን በሕይወትህ ውስጥ አድርገው። የእግዚአብሔርን ልጆች ሕዝብ ለማገልገልህ እርግጠኝነት ይሰማህ። በጎቹንና አጠቃላይ ፍጥረቱን እያገለገልክ እንደሆነ በፊትህ መታማመን ይሰማህ። አገልግሎትህ ከፍቅርና ለእርሱም ብለህ መሆኑን አረጋግጥ። በመንገድ ላይ በእያንዳንዱ እርምጃህ እግዚአብሔር እንዲመራህ ፍቀድለት። ሁሉንም ነገር ለጌታ ስትል አድርገው። በምትሠራው ሥራና በእግዚአብሔር መካከል ምንዳን ዋጋን አታስቀምጥ። ሥራህን ከእግዚአብሔር አትለይ።

የሚጠበቅባቸው ወገኖች አሉ። ሥራ ያላቸው ሥራቸውን በአግባቡ የመወጣት የሚጠበቅባቸው ወገኖች አሉ። ትምህርትና ከትምህርት ሥራ ጋር የተያያዘ ሥራ ያላቸው አሉ። ሌሎችም የተለያየ ሓላፊነት አለባቸው። ጊዜህን ለእግዚአብሔር በአግባቡ መስጠት ባይቻልህ ልብህን ስጠው። የምትሠራውን ሥራ ሁሉ በእግዚአብሔር ሥም አድርገው ፍቅሩን ማግኘት ይቻልሃል።

ሥራህን ከጌታ አትለይ። በምትሠራው ሥራ ሁሉ መካከል አብሮህ መኖሩን እርግጠኛ ሁን። በምትሠራው ሥራ ሁሉ ታማኝና ታታሪ ያደርግሃል። ዮሴፍ ታማኝና የሥራ ፍቅር የነበረው ጠንካራ ሠራተኛ ነበር። የተሰጠውን ኃላፊነት ቅዱስና ከእግዚአብሔር የተሰጠው እንደሆነ ተመለከተ። ሕዝቡን ይመግብ ዘንድ እግዚአብሔር በግብጻውያን ላይ ሞገዚት አድርጎ እንደሾመው አስተዋለ። እግዚአብሔርን በምትሠራው በማንኛውም ሥራ አካል አድርገው። የምትሠራው ሥራ እንደፈቃዱ እንዲከናወንልህ አወያየው። ቃልን ከመናገርህ አስቀድመህ በመዘመር እንደተጻፈ ጸልይ። «አቤቱ ከንፈሮቼን ክፈት። አፌም ምስጋናህን ያወራል።» በል /መዝ ፶፩፥፲፭/።

እግዚአብሔር አንደበትህን እንዲከፍትም፣ እንዲቆጣጠርም ጸልይ። በራስህ ማስተዋል ቃልን አትናገር። አንዳንዶች ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር ሌሎችን በማገልገል ይገልጹታል። ሌሎችን በማገልገል የሚገለጽ አገልግሎት ለመንግሥተ ሰማያት ሲባል የሚሰጥ አገልግሎት ነው። በእርግጥ ለእግዚአብሔር ሲባል የሚሰጥ አገልግሎት፣ ለሰው ልጆች በተለያየ ምክንያት ከሚሰጠው አገልግሎት ይለያል። የሁለቱ ዓለማት አገልግሎት የተለያየ ነው። የእግዚአብሔር ሥራ በእግዚአብሔር ፈቃድና በቅድስና የሚሠራ ነው። አገልግሎቱም በሙሉ ልብ በከፍተኛ ጥላሳት፣

Scanned by CamScanner

ስታነብ በፍቅር ከተመላ ልብ ነው? የእግዚአብሔር ወዳጅ ሆነህ ጊዜህን ከእርሱ ጋር እያሳለፍህ ነው? እርሱስ በአንተ ውስጥ ለመኖሩ ልምዱ አለህ? ወይንስ እግዚአብሔር ለአንተ እንግዳ ነው? ከሰማየ ሰማያት በላይ የራቀ ነው? በሰማይ ማደሪያው ያለነው? ከእርሱ ጋር ግንኙነት የለህም? እንዲህ አይሁን ተወዳጅ ሆይ::

አንተ ሰማያትን ሰንጥቀህ አፍአዊ ገደቦችን ሁሉ አልፈህ ወደ እግዚአብሔር ዘንድ መሔድ ወይም እርሱ አንተ ወዳለህበት ወደ ምድር እንዲመጣ ማድረግ ይጠበቅብሃል:: ዋናው ነገር አንተ በእርሱ ውስጥ መኖርህ ነው:: እርሱም በአንተ ውስጥ መኖሩ ነው:: በዚህ ዓመት መጀመሪያ ላይ መታገል የሚኖርብህ ይሄንን መንፈሳዊ ትግል ነው:: በልባችን ውስጥ የእግዚአብሔርን ፍቅር ልንተክል ይገባል:: እግዚአብሔር ለእኛ ሁሉንም ነገር መሆኑን እንገነዘባለን:: ልብን የሚሞላ፣ አእምሮን የሚቆጣጠር ስሜታችንን የሚያቀጣጥል እርሱ ነው:: ውዳቸንም፣ ጉጉታችንም፣ ፍላጎታችንም፣ መሻታችንም ነው:: ፍቅርህ በጠንካራ መሠረት ላይ የቆመ መሆኑን እርግጠኛ ሁን:: ነገር ግን አንድ ነገር አስጠነቅቅሃሁ:: ፍቅርህን በጠንካራ መሠረት ላይ ከእግዚአብሔር ጋር መገንባትህ ሰይጣን እንዳይዋጋህ አያደርግህም:: ከጸሎት በኋላ እንኳን በልብህ የሚበቅሉ አዳዲስ ነገሮች ይመጣሉ፣ ነገር ግን በጽናት ተዋጋቸው::

ሕይወታቸውን በሙሉ ለእግዚአብሔር ፍቅር ሲሉ አሳልፈው የሰጡ አንዳንድ ወገኖች አሉ:: በፍጹም ነፍሳቸውና ሐሳባቸው ያመልኩታል:: አንዳንዶች ደግሞ በዚህ ዓለም ብዙ ነገሮች ሐሳባቸው የተያዘ ነው:: ሁሉም የሰው ልጅ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ እንዲሰጥ አንጠብቅም:: ቤተሰብ ያላቸው ለቤተሰባቸው ጊዜ መስጠት

Scanned by CamScanner

ካፍሴ የመጀመሪያህ

እንዲመላለሱ አልፈቅድም በል። እኔ ፈጽሜ የእግዚአብሔር ነኝ። እርሱም የእኔ ነው። እግዚአብሔር ዕጣ ፈንታዬ ነው። እኔ የእግዚአብሔር እንጂ የማንም አይደለሁም በል። ዓለምና ፍላጎቱ ያልፋሉ። ዓለምንና የዓለም የሆነውን ነገር ሁሉ እንዳንወድ» /፩ኛዮሐ፪፥፲፯/ ቅዱስ መጽሐፍ ያስጠነቅቀናል። ራስህን ለመመርመር፣ ለማሰላሰል፣ ለማውጣትና ማውረድ ጊዜ ስጥ። በራስህ ላይ የምታደርገውን ነገር ከፍቅር እንጂ፣ ከጫና አታድርገው። ፍላጎትና ተነሣሽነት ሳይኖርህ አትጸለይ። መጽሐፍ ቅዱስን ያለመረዳት አታንብብ። አምልኮም ቢሆን መሥዋዕትም ቢሆን ያለ ሙሉ ልብና ፍቅር ትርጉም አልባ ነው።

1.9. ሁል ጊዜም ከጌታ ጋር መሆንህን እርግጠኛ ሁን

መንፈሳዊ ነገሮችን ዕለት ዕለት ማድረግህን ለመቆጣጠር ቀን መቁጠሪያህን መመርመሩ ራይዳ የለውም። ለእግዚአብሔር ተቀጥሮ ዋጋ እንደማይቀበል የልማድ ሠራተኛ ያደርግሃል። እግዚአብሔር እንደ ሱፐርቫይዘር አድርጎል፣ አላደረገም ብሎም የሚቆጣጠርህ አይደለም። ልክ በሥራ ቦታ ያሉ ሓላፊዎች እንደሚያደርጉት። አምላካችን ሰውን ወዳጅ አምላክ ነው። ፍቅሩ ወሰን ልክና ዳርቻ ስለሌለው ሰውም ያለገደብ ያፈቅረው ዘንድ ይፈልጋል። እንዲህ ከሆነ ቅርጻዊና ደንብ የበዛበት ነገር በዚህ ቦታ ዋጋ የለውም፣ ፍቅር እንጂ።

ለእግዚአብሔር ያለኝ ፍቅር ወሰኑ ምን ያህል ነው? ብለህ ራስህን ጠይቅ። የምትፈጽማቸው መንፈሳዊ ልምዶችህ በፍቅር የተመሉ ናቸው? ጸሎትህ የፍቅር ጸሎት ነው? የምትጸመው ለጌታ ካለህ ፍቅር የተነሣ ነው? ስግደትህ በፍጹም ፍቅር ራስህን በእግዚአብሔር ፊት ለማዋረድ ካለህ ስሜት የሚመነጭ ነው? መጽሐፍ ቅዱስ

Scanned by CamScanner

እግዚአብሔር ይህንን ዓለም ሲፈጥር መልካምን እንጂ ክፉ ነገርን የፈጠረ ባለመሆኑ፣ ክፋት፣ ኃጢአት አብረው የተፈጠሩ ነገሮች አይደሉም። ክፋት እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው የነጻ ፈቃድ ውጤት ነው።

1.8. ነፍስህ በጽድቅና በመልካምነት መንገድ መጓዟንም ተከታተል

ከቅዱሳን አንዱ አባ አሮ ደቀ መዝሙሩን አዘውትሮ እንዲህ ይለው ነበር። «ልጄ ሆይ ተመልከት። ወደዚህ በዓት እንግዳ የሆነ ቃል እንዲገባ አትፍቀድ። ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ጊዜውን እንዲያሳልፍ ይፈቅድ ነበር። በሐሳቡም፣ በልቡም ለአምላኩ ከነበረው ፍቅር ውጭ ሌላ ነገር አልነበረውም። እንግዳ የሆነ ነገር ወደልቡ እንዲገባ አይፈቅድም። አእምሮው መንፈሳዊ ከሆነው ነገር ውጭ እንግዳ ነገርን አያሰላስልም። ወደ ጭንቅላቱ ምንም ዓይነት እንግዳ ሐሳብ እንዲገባ አይፈቅድም። እንደዚህ ዓይነት ሐሳቦችን፤ እንግዳና ባዕድ በማለት ይጠራቸዋል። ወደ በዓትህ እንግዳ የሆነ ቃል እንዲገባ አትፍቀድ»

እንግዳ የሆነ ርዕስ፣ ጽድቅም ያልሆነ ሐሳብ፣ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ነገር መንገድ መጀመሩን ስትመለከት ከንደኛህ ጋር ልትወያይበት የሚገባ የእግዚአብሔር ቃል መኖሩን አስታውስ። እንዲህ የሚለውን የነቢዩን ቃል ፈጥነህ ወደ ልብህ አምጣ። «እንግዶች ቁመውብኛልና ኃያላንም ነፍሴን ሸተዋታልና። እነሆ እግዚአብሔር ይረዳኛል።» /መዝ ፶፬፥፬/።

ነፍስህን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ሞክር። በግንኙነታችሁ ባዕድ ነገር አይግባ። ልብህን ፈጽመህ ለጌታ ለመስጠት ወስን። «እኔ የውዴ፣ ውዴ የእኔ በመሆኑ ባዕድ የሆኑ ሐሳቦች በአእምሮዬ

Scanned by CamScanner

ስለዚህ ሰው ሆይ መልካምነትና ጽድቅን ከወደድህ ራስህን በጥንቃቄ መርምር፤ /አሳብህን ፈትሽ፤ እሴቶችህን ዕወቅ:: የምትመራበትን የሕይወትህን ፍቅር በልቡናህ ውስጥ አኑር:: መልካምነትን ከወደድህ የእግዚአብሔር ፍቅር በልቡናህ ውስጥ ይበቅላል:: እግዚአብሔርንም ከወደድኸው ወደ መልካም ነገር ሁሉ ይመራሃል:: የትኛው መቅደም አለበት ብለህ ብታስብ በእርሱ ብዙ አሳብ አይግባህ:: ወደሌላው የጽድቅ መንገድ ሊመራህ ከሚችለው ከአንዱ መንፈሳዊ ጥበብ መጀመር ትችላለህ:: ተቀባይነት ያለው ሞራላዊ እሴቶች ያሏቸው አጠቃላይና ጥብቅ የሆነ የሕይወት መርሕን ለሚከተሉ ወገኖች የእግዚአብሔርን መንገድ ለመከተል ቀላል ይሆንላቸዋል::

እግዚአብሔርን በእውነትና ከልብ ስትወደው በልብህ ውስጥ ሥፍራ እንዲኖረው የምትፈቅደው ባዕድ ነገር አይኖርም:: ከእግዚአብሔር ፍቅር የሚያርቅህ ማንኛውም ባዕድ የሆነ ነገር እንግዳና ከተቀደሰው ተፈጥሮህ በተቃራኒ ያለ ነው:: «ይህ ተፈጥሮዬ ነው» የሚለኝ ሰው ሲያገጥመኝ አንዳንድ ጊዜ እደነቃለሁ:: ሲናደድና አላስፈላጊ የሆነ የስድብ ቋንቋን ከአንደበቱ እያወጣ «እኔ ደካማ ነኝ ይላል:: በእርግጥ የሰው ተፈጥሮ ቅዱስ ነው:: እግዚአብሔር ክፉ የሆነ ባሕርይን በሰው ውስጥ አላስቀመጠም:: ክፉ ነገር ለአንተ ተፈጥሮ ባዕድ ነው፤ እንግዳም ነው:: የተፈጥሮህ ባሕርይህ አካል አይደለም:: ቅዱስ የሆነውን ተፈጥሮህን የወረረ ጥገኛ ሕዋስ ነው:: እነዚህን በሰውነትህ ውስጥ የበቀሉ እንግዳ የሆኑ አረሞችን ነቅለህ ልትጥል ይጠበቅብሃል:: ይህ ያልተለመደና አርቶዶክሳዊ ያልሆነ ባሕርይ ነው:: ነፍስህን የበሳነትን መንገድ እንድትከተል ፍቀድላት:: እርግጠኛ ሁን የትኛውንም ያህል ኃጢአት ቢዋጋህ ተፈጥሮህ መልካምና ቅዱስ ነው::

Scanned by CamScanner

ፈቃድ ስትፈጽም እግዚአብሔር በዚያ ሥፍራ የለም ማለት ነው። ያለው በውጭ ነው። ይህም ማለት ልብህ እልከኛና የማታይታዘዝ ነው ማለት ነው። ስለዚህ በተሳሳተ ጎዳና ላይ ነህ። በተመሳሳይ ንግግር የተወሰነ ሰዓት ለእግዚአብሔር ስትሰጥ የልብህን ፈቃድ አትከተልም ማለት ነው።

በመጨረሻም አስቀድመን ያነሣው አባባል የሚያመለክተው መንሸራተትና መዋገቅ በሰው ሕይወት የሚከሥት አደጋ መሆኑን ነው። ይህም የታወቀ አቅጣጫ፣ ግልጽ የሆነ ራእይ፣ የጠራና ግልጽ የሆነ ዓላማ ካለማስቀመጥ የሚነሣ ነው። ጌታ «ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ ይላል እርሱም በፍቅር ጥብቅ የሆነ ነው።»

እግዚአብሔርን ካላወቅኸው ልትወደው አትችልም። አንድ ሰው ኃጢአትን ሊወድና ከእርሷም ጊዜያዊ ደስታን ሊያገኝ ይችላል። እግዚአብሔር ወደዚያ አቅጣጫ እንደገፋው ሊያስብም ይችላል። በዚህ ሁሉ ነገር መካከል እግዚአብሔርን ሊወደው ይችላል። ነገር ግን የፍቅር መንገዱ ይሔ አይደለም። ለእግዚአብሔር ያለህ ፍቅር እውነተኛና ከልብ የሆነ መሆን ይገባዋል። ኃጢአትን ወደህ ወደ እግዚአብሔር ለመሳብ መንገድ እንደሆነ አታስብ። ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር አታቀላቅለው። ቁጣውንና መቅሠፍቱንም በመፍራት አይደለም ኃጢአትን መሸሽ የሚጠበቅብህ። ይህም ረብህና ጥቅም የሌለው ነገር ነው። ጽድቅንና መልካምነትን ካልወደድህ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አይቻልህም።

በዚህ ዓለም እግዚአብሔር የለም የሚሉ ወገኖች፤ እግዚአብሔር የለም የሚለብት ምክንያት ዓለማዊ ፍላጎታቸውን ያለ አጥርና ያለ ከልካይ እንዳይፈጽሙ እግዚአብሔር እንቅፋት እንደሆነባቸው በማሰባቸው ነው። ስለዚህም ምክንያት እግዚአብሔርን ይጠሉታል።

Scanned by CamScanner

YBM Construction Management Co
Project information

ነፍሴ የመዳድችህ

ደቀመዛሙርት በመሪነት ፍቅር ልባቸው ተይዞ ነበር። የመጀመሪያ ለመሆን የነበራቸው ምኞት የዮሴፍ ወንድሞች ወንድማቸውን እንዲሸጡ፣ የጌታ ደቀመዛሙርት የማይገባቸውን እንዲለምኑ ምክንያት ሆኗል። ዓለምን መውደድና የሥጋ ፍላጎት ልብን ይቆጣጠራል። በልብህ ውስጥ እየዳኸ ያለው ነገር ምንድነው? ለእግዚአብሔር ያለህን ፍቅር ምን ቀማህ? በልብህና በነፍስህ እንግዳ የሆነ የእግዚአብሔርን ሥፍራ የያዘ ነገር አለን? ራስህን ጠይቅ።

እግዚአብሔርን መውደድ ለአዲስ ኪዳን ብቻ የተሰጠ ትእዛዝ አይደለም። በብሉይ ኪዳን ዘመን ፡ አስቀድሞ የተገለጠ ነው እንጂ። በዘዳግም «አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ኃይልህ ውደድ» /ዘዳ ፮፡፭/ ተብሎ ተጽፏል። እግዚአብሔርን ከልብህ ውደድ ተብሎ የተጻፈ ተራ ሕግጋትም አይደለም። እንደ እርሱ ቢሆን ቀላል በሆነ ነበር። በፍጹም ልባችን እንድንወደው የተጻፈ ትእዛዝ ነው እንጂ። በሌላ አነጋገር ልባችን በሙሉ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ነው። ስለዚህ ስብከትን እንደመዝናኛ በሚቆጥሩ ሰባክያን ዘንድ የተለመደ አባባል «አንድ ሰዓት ለልብህ፣ አንድ ሰዓት ለእግዚአብሔር ስጥ» የሚለው ተቀባይነት የለውም። ትክክል ያልሆነና ወደ ስሕተት የሚመራ ነው። ብዙ ዓይነት ስሕተቶችንም ይዟል። በመጀመሪያ ሰው ለእግዚአብሔር ሊኖረው የሚገባው ፍቅር ተለዋዋጭ ይሁን እንደማለት ነው። ቀኑን የራስህን ፍላጎት በማሟላት አሳልፎ ሌላ ጊዜ እግዚአብሔርን አምላክ እንደማለት ነው።

በሁለተኛ ደረጃ በእግዚአብሔርና በልባችን መካከል ክፍፍል ፈጥሯል። አንድ ሰዓት ለእግዚአብሔር፣ አንድ ሰዓት ለልባችን ማለት ልብ ከእግዚአብሔር ጋር የለም ማለት ነው። በዚህን ጊዜ የልብህን

Reported to(Project Mgt. Consultant
Name
Signature
Date
Habtamu.M
08/05/2021
Signature
Date

Scanned by CamScanner

ከዛፉ መብላቱ በጣም ግልጽ ከባድ የሆነ የሚያስተላልፈው መልእክት ነበረው። የአዳም ችግር ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር የሚጋጭ በተቃራኒ ያለ ነገር ወደ ልቡናው ተሰርቆ መግባቱ ነበር። በፍጹም ልቡ በሚወደው በአምላኩ ቦታ እንግዳ የሆነ ነገር ቤት ለእምቦሳ ማለቱ ነው። በፍቅር ሥፍራ አድመኝነት ወደ አዳም ልቡና ተሰርቆ ገባ። እርሱም ለአዳም እንግዳ የሆነ የዕፅ በለስ ፍቅር ነበር። በአዳም ልብ ውስጥ አዲስ ፍቅር መዳህ ጀመረ። በእርግጥ የዕውቀት ፍቅር ነበረን? ኩራት ነበረን? ከእግዚአብሔር ጋር እኩል የመሆን ፍላጎት ነበረን? ምንም ይሁን ምን በእርግጠኝነት ውጫዊና እንግዳ የሆነ ፍቅር ነበር። ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር እኩል ለመሆን የሚታገል አዲስ ፍቅር በልቡናው ነበር።

1.7. ለእግዚአብሔር ያለህ ፍቅር እውነተኛና ከልብ የሆነ መሆን ይኖርበታል

ራስህን እንዲህ ብልህ መጠየቅ ይኖርብሃል። «በልቤ ውስጥ እየዳኸ የሚመጣ፣ ታላቅ፣ ከእግዚአብሔር ፍቅር በተቃራኒ ያለ ፍቅር በእኔ ውስጥ አለ? ሁላችንም እንደምናውቀው የሰዶም ፍቅር፣ አረንጓዴነቷም፣ ግልጽ ውበቷም የሎጥን ልብ ምን ያህል ተቆጣጥሮት እንደነበረ ነው። ሶምሶን ለደሊላ የነበረው ፍቅር እንግዳና ያልተለመደ ነበር። ሶምሶን ለእግዚአብሔር ከነበረው ፍቅር የበለጠ ሆነ። የግንዘብ ፍቅር በሐናንያና ሰጲራ ልብ ውስጥ የነበረውን የእግዚአብሔር ሥፍራ ቀምቷል። ንጉሥ ሳያል በግል ዝና፣ በሥልጣን መውደድ፣ ለግል ስሙም ክብር በነበረው ጉጉት ተፈትኗል። በዚህም ምክንያት ንጉሥ ዳዊትን አስቀይሞታል። የዮሴፍ ወንድሞችና የጌታ

Scanned by CamScanner

ነፍሴ የመደደችህ

እምላለሁ »የሚለውን /ፎኛ ነገሥ ፲፮፥፱/:: ነቢዩ ኤልያስ ሁልጊዜም በእግዚአብሔር ፊት መቆሙን ያስባል:: እግዚአብሔር በሁሉም ሥፍራ ያለ ነው:: በመንገዱ ላይ እግዚአብሔር ቆሟል:: በሐሳቡም፣ በሥራውም፣ በምግባሩም፣ በመውጣቱ፣ በመግባቱም እግዚአብሔርን ዘወትር ይመለከተዋል:: በማንኛውም ሁኔታ ኤልያስ በእግዚአብሔር ፊት ቆሟል:: ነቢዩ ዳዊትም የተናገረው ቃል «ሁል ጊዜ በፊቴ አየዋለሁ:: በቀኜ ነውና አልታወከም::» የሚለው ተመሳሳይ ነገርን ያስታውሰናል /መዝ ፲፮፥፰/::

1.5. *እግዚአብሔርን እንዴት መውደድ እንዳለብህ? እንዴት በቅንዓት መጸለይም እንደሚገባህ? ማወቅ አለብህ*

እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ፍጹም ፍቅርህን ነው:: ይህን ማድረግ ወይም አለማድረግ የሚል ቃል አያስጨንቅህ:: እርሱ እግዚአብሔርን አያስደስተውም:: ራስህን ነጻ አድርግ:: የሕግ ትእዛዛትን፣ የፍቅር ትእዛዛትን አድርገህ ተቀበል:: በፍቅር ከተመላለስህ ራስህን በሕጉና በትእዛዙ ውስጥ ታገኘዋለህ:: መጽሐፍ ቅዱስ የሚያዘውን፣ ከዚያም አብዝተህ መፈጸም ይቻልሃል:: ፍቅር ተፈጥሮህን ያድሳል::

1.6. «ውዴ የእኔ ነው፣ እኔም የእርሱ ነኝ

ራስህን በእውነት ለእግዚአብሔር አሳልፈህ ከሰጠህ፣ እርሱ ያንተና ካንተ ጋር ከሆነ፣ ከእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ በተቃርኖ እንድትቆም የሚያደርግህ ነገር የለም:: ከእግዚአብሔርም የበለጠ የምትወደው አንዳች ነገር አይኖርህም:: የአዳም ኃጢአት ምን ነበር? መልካምንና ክፉ ከሚያሳውቀው ዕፅ መብላቱ ነውን? አይደለም::

08/09/21	Signature	Habtamu.M	Reported to(Project Mgt. Consultan
	Date	08/05/2021	Name
			Signature
			Date

Scanned by CamScanner

ለእግዚአብሔር ያለህ ስሜት ይህ ዓይነት መንፈሳዊ ግለት ቅናትና ትጋት ያጀበው ነው? ወይንስ የጎደለ? እግዚአብሔር በሰማየ ሰማያት ውስጥ የተሰወረ ከአንተም የራቀ ነው? ከርሱም ጋር በነፍስህ ግንኙነት የሌለህ ባእድ አካል ነው? ከሰማየ ሰማያት በላይ ሩቅ ነው? ግንኙነት የለህም? እግዚአብሔርን እንዴት መውደድ እንዳለብህ ማወቅ ይኖርብሃል። በስሜትና በጉጉት እንዴት መጸለይ እንዳለብህ ተማር። ለእግዚአብሔር የሚኖረን ፍቅር ቀጠሮ ሊበዛበት የሚገባው አይደለም። ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ግንኙነት ውጣ ውረድ ያጀበውም አይደለም። እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነት ነገርን አይፈልግም። እርሱ የሚወደው እውነተኛ የሆነ ፍቅርህን ብቻ ነው። «ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ፤ ዓይኖችህም መንገዴን ይከተሉ።» /ምሳ ፳፫፥፳፮/ ይላል። እግዚአብሔር ከአንተ ጋር በሚኖረው ግንኙነት ከአንተ የሚፈልገው ይሄንን ነው።

እግዚአብሔርን መውደድ ስትጀምር እግዚአብሔር በልብህ ሥፍራ እንዳለው አንተም በእርሱ ልዩ ስፍራ እንዳለህ ትረዳለህ። በግንኙነትህ ሁለትዮሽ የሆነ ጥብቅ የፍቅር ግንኙነት መኖሩን ትገነዘባለህ። አንተ ከእግዚአብሔር ጋር እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር ነው። ከአንተ ጋር በመንገድህ ሲራመድ ትመለከተዋለህ። በእርሱ አስተማማኝ እቅፍ ውስጥ ማረፍህን ስታውቅ ደኅንነት ይሰማኻል። በመንገድህ ላይ ካለው ከማንኛውም ዕንቅፋት ሲጠ ብቅህ ታስተውላለህ።

እግዚአብሔር ከአንተ ጋር መኖሩ የሚሰማህ በዚህ ሁኔታ ነው። በዚህ ሁኔታ የነቢዩ የኤልያስን ቃል እወደዋለሁ። «በፊቱ የቆምኩትን የእሥራኤልን አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን በስሙ

ነፍሴ የመደደችህ

ስሜት አይሰማውም። አይገባውም። እግዚአብሔር ከብዙዎቹ ጋር፣ ከሀብታሞች ጋር፣ ከሚጮኹ ጋር ብቻ እንዳለ ማንም አያስብ። በፍጹም እግዚአብሔር የአንተና የአንተ ብቻ ነው። እውነት ነው እግዚአብሔር የፍጥረቱ ሁሉ ጌታ ነው። በተለየ ግን የአንተ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ግንኙነት በተለየ ለአንተ ነው።

የፍቅር ግንኙነትህ ባለህ ዝንባሌና ስሜትና ላይ ይወሰናል። በሌላ አነጋገር መንፈሳዊ ሰው የሚጸልየው እግዚአብሔርን በመፈለግና በመጠበቅ ነው። የተወሰኑ ትእዛዛት እንዲጸልይ ስላስገደዱት ብቻ ወይም ከጎሊና ወቀሳም ለማምለጥ አይደለም። ቅዱሳን የሆኑ ሰዎች እንዲጸልዩ የተጣለባቸው ሓላፊነት ስለሆነ፤ እርሱም እነርሱን ለመምሰል ሲል ብቻ አይደለም። እግዚአብሔርን ፍጹም ከመናፈቅ የተነሳ የሚጸልይ ነው እንጂ። ነቢዩ ዳዊት የሚያስታውሰን ይሄንኑ ነው።

1.4. «*ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ አቤቱ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች።*» መዝ ፵፪፥፩

አንተስ ለእግዚአብሔር ያለህ ፍቅር በዚህ ስሜት ላይ የተመሠረተ ነው? ወይንስ ለብ ካለ ስሜት የሚነሣ ትጋትና ሙቀት አልባ ነው? ወደ እግዚአብሔር ቤት ስትሔድ የደስታና የሐሴት ስሜት ይሰማኻል? «ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ።» /መዝ ፻፳፪፥፩/ ትላለህ? «ነፍሴ በኋላህ ተከታተለች» /መዝ ፷፫፥፰/ ትላለህ? ወይንስ «የልመናዬን ድምፅ አድምጥ፣ ጩኸቴን አስተውል ንጉሤና አምላኬም ወደ አንተ እጸልያለሁና በማለዳ ድምፄን ትሰማለህ፤ በማለዳ በፊትህ እቆማለሁ፣ እጠብቃለሁም። /መዝ ፭፥፩—፬/ ትላለህ።

Scanned by CamScanner

1.2. ፍቅረ እግዚአብሔር መቸም የትም ጽኑና ጥብቅ ሊሆን ይገባዋል

እውነተኛ ፍቅር ጥብቅና የማይዋዥቅ ነው። በሰው ሕይወት ውስጥ የሚከሠት ማንኛውም ለውጥ አያነዋውጠውም። አንዳንድ ጊዜ ፈተና ማለፍ የተሣነው ተማሪ እንመለከታለን። በሁኔታው ተናድዶ ከእግዚአብሔር ጋር ሲከራከር ይስተዋላል። ይህ ሁኔታ በእኔ ላይ እንዲከሠት እንዴት ፈቀድክ? ይላል። በእውነት እንነጋገር ከተባለ በእግዚአብሔር እንድንቆጣ የሚያደርገን አንዳች ምክንያት አናገኝም። ነገር ግን ግንኙነታችን እንደሚለዋወጥ ለማሳያ ያህል ያነሳሁት ነው። ወይም ለአንድ የታመመ ሰው ጸልየህ ይሆናል። ሕመሙ ካልተሻለው በልብህ ታጉረመርማለህ። እግዚአብሔር ጸሎቴን የማይሰማኝ ለምንድነው? ትላለህ። በእግዚአብሔር ትቆጣለህ። እግዚአብሔርን መውደድ ግን በማንኛውም ሁኔታ የሚለዋወጥ አይደለም። መከራም፣ አደጋም ቢሆን ፍቅራችንን የመቀነል ጨርሶም የማጥፋት ኃይል የላቸውም። እግዚአብሔርን ልትወደው የሚገባህ ሁል ጊዜ መልካም ነገርን ከእርሱ ስለምንጠብቅ ብቻ አይደለም። እርሱ እግዚአብሔር በመሆኑ ብቻ ልንወደው ይገባናል። ውጫዊ ምክንያቶች ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ አንድነት ላይ ምንም ተጽእኖ ሊኖራቸው አይገባም።

1.3. «ውዴ የእኔ ነው፣ እኔም የውዴ ነኝ»

ይህ ማለት እግዚአብሔር የአንተ፣ አንተም የእግዚአብሔር ነህ ማለት ነው። ይህ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለውን ልዩና ብቸኛ የሆነ ግንኙነት ዋና መገለጫ ነው። ሰው በዚህ ሰፊ በሆነ ዓለም ውስጥ የመጥፋት ወይም ግራ የመጋባት

Scanned by CamScanner

ነፍሴ የመጀመሪያ

«ውዴ የእኔ ነው፡ እኔም የእርሱ ነኝ ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖርህ ግንኙነት መሠረቱን ፍቅር አድርግ። ይህ አንቀጽ ፍቅር ሁለትዮሽና የጋራ መሆኑን ያሳያል። እግዚአብሔር ይወድሃል። በተመሳሳይ ሁኔታ አንተም ትወደዋለህ። «እርሱ አስቀድሞ ወድዶናልና እኛም እንወደዋለን።» /፩ኛ ዮሐ ፬፥፲፱/ ተብሎ እንደተጻፈ። እግዚአብሔር ስለወደደህ ፈጥሮሃል። ስለወደደህም ከዙሉ በሚበልጠውና ተመሳሳይ በሌለው በእርሱ መልክና ምሳሌ ፈጠረህ። መረዳትን፣ ጥበብን፣ መንፈሳዊነትን፣ ዘላለማዊነትንና በነገር ሁሉ ውበትን ሰጠህ።

ፍቅር አጸፌታዊ የተቀበሉትን መስጠት የሰጡትንም መቀበል መሆን አለበት። ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት የሚዋዥቁ ወገኖች አሉ። አንድ ጊዜ ሞቅ፣ ሌላ ጊዜ በረድ ይላሉ። ይለዋወጣሉ። አንዳንድ ጊዜ ግንኙነታቸው ጠንካራና ጥብቅ፣ ሌላ ጊዜ የላላ ነው። አንዳንድ ጊዜ ንስሐና ጸሎት የተሞላው ኑሮን ይኖራሉ። በሌላ ጊዜ ወደ ኃጢአትና ወደቀደመው መንገዳቸው ይመለሳሉ። በግንኙነታቸው ጽናት፣ መንፈሰ ጠንካራነት፣ ቆራጥነት አይታይባቸውም። መንፈሳዊ ሰው ግን ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር ቀን በቀን የሚያድግ እንጂ የሚቀጭጭ አይደለም። ወደቀደመው መንገድ ወደ ኋላ ዙሮ ማየት አይስማማውም። የፍቅር ሰው «የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና ከአፌ ልተፋህ ነው» /ራእ ፪፥፬/ ከሚለው ወቀሳ የጸዳ ነው።

08/09/21	Signature	Habtamu.W	Reported to(Project Mgt. Consul Name
	Date	08/05/2021	Signature Date

Scanned by CamScanner

ብዙ የሚጸልዩ ሰዎች አሉ። ልባቸው ግን ከእግዚአብሔር ፍቅር ፈጽሞ የራቀ ነው። በተመሣሣይ ሁኔታ የሚጸሙ ብዙ ሰዎች አሉ። ለእግዚአብሔር ያላቸው ፍቅር ግን ደካማና ጎደሎ ሆኖ ይታያል። በተመሣሣይ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያን የሚያዘወትሩ፣ በንስሐ የሚኖሩ በቅዱስ ሥጋውና ደሙ የተወሰኑ፣ በተለያየ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሳተፉ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ያላቸው ፍቅር ፍጹም ያልሆኑ ወገኖች አሉ።

በአጭሩ ከእግዚአብሔር ጋር ያለ እውነተኛ ግንኙነት እግዚአብሔርን መውደድ ወይም አለመውደድህ የሚለካበት ነው። በሌላ አባባል እግዚአብሔርን ምን ያህል እወደዋለሁ? የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል። እግዚአብሔርን የምትወደው ከሆነ፣ ጸሎት ለዚህ ፍቅር ተፈጥሮአዊ መገለጫው ነው። ጾምም እንዲሁ። ለእግዚአብሔር ያለህ ፍቅር ረሃብንና ለምግብ መስገብገብን የመሳሰሉ ዓለማዊ ፍላጎትህን ሁሉ ከንቱ አድርጎ ያጠፋልሃል። እግዚአብሔርን ሳይወዱት እንደሚጸሙ ወሮኛ ሳይሆን፣ ጾምህ የሚሥሠው ከእውሩኛ የልብ ፍቅር ይሁን።

ለምሳሌ በሕንድ ማጎበረሰብ ዮጋ የተባለ የጾም ልምምድ እንዳለ ብዙ አንብቤአለሁ። እርሱም ራስን ለመግዛት፣ ለሥነ ሥርዓትና ለጤና ሲባል የሚደረግ ልምምድ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ጾም ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር የሚያገናኘው አንዳች ነገር የለም። ለእግዚአብሔር ካላቸው ፍቅር የተነሣ በሚጸሙና እግዚአብሔርን ፈጽሞ ሳያስታውሱ ራስን ለመቆጣጠርና የሆነ ደረጃ ላይ ለመድረስ ብቻ ጾምን በሚጸሙ ወገኖች መካከል እጅግ የገዘፈ ልዩነት አለ።

Scanned by CamScanner

ነፍሴ የመደደችህ

ከእውነተኛ ፍቅር የሚመነጭ መታዘዝን ከሰው ልጆች ይፈልጋል። ስለዚህም ምክንያት መድኃኒታችን «ከወደዳችሁኝ ትእዛዜን ጠብቁ»ይላል /ዮሐ ፲፬፥፲፭/። ይህም ማለት የእግዚአብሔርን ትእዛዛትና ሕግጋት መጠበቅ ከእውነተኛ ፍቅር ሊመነጭ የሚገባው እንጂ፣ እንዲሁ ልማዳዊ ከሆነ መታዘዝ የሚነሣ መሆን አይገባውም ማለት ነው።

አንዳንድ ወገኖች ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት በፍርሃት ላይ የተመሠረተ ነው። ነፍሳቸውን በሲያልም፣ በሽኮመ እሳትም ሊቀጣ እንደሚችል በማሰብ ይፈሩታል። የእግዚአብሔር መቅሠፍቱንና መዐቱን ይፈራሉ። ፍርሃት ግን የእርሱ ጻድቃንና ቅዱሳን ለሆኑት ለእግዚአብሔር ልጆች የሚመጥን ጤናማ የሆነ መንፈሳዊ ደረጃ አይደለም። በእርግጥ ፍርሃት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ላለው ግንኙነት መሠረት ነው። ሰው ግን መሠረቱ ፍቅር እንጂ ፍርሃት ብቻ አድርጎ ሊዘልቅ አይገባውም።

ሰው በመጀመሪያ ሕጉንና ትእዛዛቱን በመጠበቅ ግንኙነቱን በፍርሃት ይጀምራል። በፍቅር ይፈጽማል። ይህንን ደረጃ ካለፈ በኋላ ሕጉንና ትእዛዛቱን የሚፈጽመው ከፍቅር እንጂ ከፍርሃት አይሆንም። ሌሎች ወገኖች ከጌታ ጋር ያላቸው ግንኙነት ልማድን መሠረት ያደረገ ነው። በሌላ አገላለጽ ሲጸልዩ፣ ሲጾሙ፣ ቤተ ክርስቲያን አዘውትረው ሲሔዱ፣ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ሲቀበሉ ይስተዋላል። ነገር ግን የፍቅር ድርቅ የመታቸው ናቸው። እርግጠኛ ሁኑ ጸሎት ያለ ፍቅር ባዶና ትርጉም አልባ ነው። እውነተኛ ጸሎት ለእግዚአብሔር ካለን ፍቅር ከርሱም ጋር ለመኖር ካለን ናፍቆት የሚነሣ የእውነተኛ ፍቅር ነጸብራቅ ነው።

9/09/21	Signature	Habtamu.M	Reported to(Project Mgt. Consultants Name	
	Date	08/05/2021	Signature	
			Date	

Scanned by CamScanner

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

ክፍል አንድ

ምዕራፍ አንድ

1.1. ውዴ የእኔ ነው እኔም የእርሱ ነኝ መኃ ፪፥፲፮

በአዲሱ ዓመት መጀመሪያ በጣም ጠቃሚ ስለሆነ ጉዳይ አንሥቼ ከእናንተ ጋር መወያየት ወደድሁ። እርሱም ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነትን የሚመለከት ነው። ሁላችንም መልካም የሆነ ጅምር ይኖረን ዘንድ፣ ስለዚህም ምክንያት ከመዝሙራት ሁሉ ከሚበልጠው የሰሎሞን መዝሙር የሚከተለውን ኃይለ ቃል ወሰድሁ። የሰው ነፍስ ከአምላኳ ጋር ያላትን ግንኙነት የሚያስረዳውን አንቀጽ «ውዴ የእኔ ነው እኔም የእርሱ ነኝ። በሱፍ አበባዎች መካከል መንጋውን ያሰማራል /መኃ ፪፥፲፮/።

«ውዴ የእኔ ነው፣ እኔም የውዴ ነኝ የሚለው ኃይለ ቃል በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነት፣ የፍቅር ግንኙነት መሆኑን ያመለክታል። ብዙ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት በመታዘዝ ይጀምራል። በዚሁ ላይ ይቆማል። ሰው በእርግጥ የእግዚአብሔርን ሕግጋትና ትእዛዛት መፈጸሙ መልካም ነው። ነገር ግን መታዘዝ ፍቅር የጎደለው ከሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም። ሕጉንና ትእዛዙን ጠብቀህ ኃጢአትን ማስወገድ ይቻልሀ ይሆናል። ነገር ግን በዚህ እግዚአብሔርን አንኳን አትወድደውም። ውጫዊ /በአፍአ/ የሆነ ታዛዥነት ብቻውን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም። እግዚአብሔር

Scanned by CamScanner

ተገንዝቦ መጓዝ አስፈላጊ ነው። ወደ ጌታ የምናደርገው ጉዞ መንፈሳዊነታችንን ለመረዳት በሕይወታችንም እኒህ ነገሮች እንደሚፈራረቁ በማወቅ በመጨረሻ ወደ አሰብነው ግብ እንደርሳለን።

ብፁዕ ቅዱስ አባ ሺኖዳ 117ኛው የመንጌላዊው ቅዱስ ሐዋርያው የማርቆስ መንበር ፓትርያርክ ናቸው። የግብጽን ቤተ ክርስቲያን ከጎዳር 14 ቀን 1971 ዓ.ም እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው ድረስ በፓትርያርክነት መርተዋል። ቤተ ክርስቲያኗን ከሕዛንነት ዕድሜያቸው ጀምረው አገልግለዋል። ከ100 በላይ የሚሆኑ መጻሕፍትን ጽፈዋል። ብዙዎቹም በዐረብኛ፣ በእንግሊዘኛ፣ በፈረንሣይ፣ በስፓኒሽ፣ እንዲሁም በጀርመን ቋንቋዎች ተተርጉመዋል። ልዩ የሆነ የንግግር ተሰጥዖ ነበራቸው። በእነዚያ ጊዜያት በርካታ የሆኑ «ሊታረዱ የተወሰነባቸውን ነፍሳት ከሕይወት ወደ ሞትም የሚነዱትን» ብዙዎችን መልሰዋል።

የዚህ መጽሐፍ ተርጓሚም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ እንደ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሊሉ እንደሚገባቸው ያምናል፦ «እኔ ግን ፈጽሜ ግዳጄን ፈጽሜአለሁ። መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፤ ፉጫዬንም ጨርሻለሁ፤ ሃይማኖቴንም ጠብቄአለሁ። እንግዲህስ የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶኛል፤ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው እግዚአብሔር በዚያ ቀን ለእኔ ያስረክበል። ደግሞም መግለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።» /፪ኛ ጢሞ ፬፥፮—፮/

ይህ መጽሐፍ ዐሥራ ስድስት ምዕራፎች አሉት። የመጽሐፉን መሠረተ አሳብ ለመረዳት ሁሉንም የንባብ ክፍሎች ማንበብ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው እላለሁ፤ ትምህርቶቹን በመተርጎምና በመጽሐፍ መልክ በማዘጋጀት ለንባብ ያበቃው በቦስተን የሚገኘው የኮፕት ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ነው።

ዲ/ን ታደለ ፈንታው

Scanned by CamScanner

እንዲሳለበት፣ በጎሊና ክንፍ ተሞሞ ነፍሱ የአባቶቹን ድካም እንዲ ያደንቅ አድርገውታል። አንባቢውን ጥያቄ ይጠይቁታል። ራሱ እንዲ መልስ በብዙ ምሳሌዎች ያቀርቡታል። ነፍስ ያለችበትን ሁኔታ እንድንመረምር ከእርሳቸው ጋርም እንድንጓዝ ይጋብዙናል።

አቡነ ሺኖዳ አንድን ምዕራፍ ሲጀምሩ የተወሰኑትን የመጋልየ መጋልይ ክፍሎች ይወስዳሉ። ይህም ክርስትናና ያለውን አጠቃላይ መልክ በተጨባጭ ለመግለጽ የተጠቀሙበት መሣሪያ ነው። እያንዳንዱን ምዕራፍ የሚጨርሱት በጸሎት ነው። በዚህም እያንዳንዱ አንባቢ ነፍሱ ከወደደችው አምላኩ ጋር ቅርብ የሆነ ግንኙነት እንዲኖረው ይመሩታል። በእያንዳንዱ ምዕራፍ የተሰፋ መልእክት በስፋት ይንጸባረቃል። የክርስቶስን መንጋ ወደ መንጋው እረኛ ወደ ክርስቶስ እንዲጠጋ ያበረታቱታል።

የዚህ መጽሐፍ ተቀዳሚ ዓላማ የሰው ነፍስ አምላኳን ለመፈለግ በምታደርገው ጉዞ ግራና ቀኝ እየተመለከተች፤ በእርጋታ ነገር ግን በመንፈሳዊ ፍጥነት በጽሞና ማሰላሰል የሚገባት መሆኑን ማመልከት ነው። ነፍስ ወደ ፈጣሪዋ የምታደርገው ጉዞ የተለያዩ ወቅቶች አሉት። ቅዱስነታቸው እንደሚሉት መንፈሳዊ ሕይወትን በተመለከተ ልብን የሚነካ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በአሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ስምንት የሚገኘው የመጨረሻው አንቀጽ ነው። ይኸውም «በምድር ዘመን ሁሉ መዝራትና ማጨድ፣ ብርድና ሙቀት፣ በጋና ክረምት፣ ቀንና ሌሊት አያቋርጡም።»/ዘፍ፲፥፳፪ / የሚለው ነው። በሰው ሕይወት ውስጥ ይህ ሁኔታ በስፋት አለ። በሕይወታችሁ ቀንና ሌሊት አለ፣ ሙቀትና ቅዝቃዜ አለ፣ ክረምትና በጋ አለ። ወደጌታ በምናደርገው ውጣውረድ የበዛበት ጉዞ ይኸንን ሁኔታ እንዳለ

Scanned by CamScanner

ካፍሌ የመጀመሪያ

መግቢያ

ብፁዕ ወቅዱስ አባ ሺኖዳ በአስቂጥስ በረኃ የምናኔ ሕይወትን እየመሩ በነበሩበት ወራት የነበራቸውን የተመስጠ፣ የጥልቅ ንባብና የጸሎት ሕይወት ተጠቅመው የሰው ነፍስ ልትከተለው የሚገባውን ጉዞ በተመለከተ ጠቃሚ መጻሕፍትን በዘመኑ ለምንገኝ ክርስቲያኖች አበርክተውልናል። ቅዱስነታቸው በጌታችን በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለንን ትውክልትና መታመን፣ እምነትና ተስፋ የሚያመላክት አሻራን ትተውልን አልፈዋል። ከሰንበት ትምህርት ቤት እስከ ታትርያርክነት ድረስ በተዘረጋው የአገልግሎት መንገድ ያካበቱትን ዕውቀትና ልምድ ሁላችንም ልንረዳው በምንችለው ቋንቋ፣ በቀላል አቀራረብም አቅርበውልናል።

የዘመናችን የቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፍት ቅዱስ አባ ሺኖዳን በተለያየ ስም ይጠሩአቸዋል። እውነተኛው እስክንድርያዊው አቡነ አትናቴዎስ፣ የቀሌሜንጦስ፣ የቄርሎስና፣ የዲዮስቆሮስ አልጋ ወራሽ በማለት ይጠሩዋቸዋል። ከ50 ዓመታት በላይ ያስቆጠረው የምንኩስና ሕይወታቸው፣ ለክርስቶስ ያላቸውን ፍጹም እምነት፣ ከክርስቶስ ጋር እውነተኛ የሆነ አንድነት የምትፈልግ ነፍስ የምትጓዝበትን ውጣ ውረድ፣ የሚያጋጥማትን ፈተና፣ የምትካፈለውን ደስታ፣ ከድካሚ የምታገኘውን ዕረፍት አምልተው አስፍተው እንዲጽፉልን አስችሏቸዋል።

ይህ መጽሐፍ ብፁዕነታቸው በ1970ዎቹ ካስተማሯቸው ተከታታይ ትምህርቶች የተወሰደ ነው። አቀራረቡም ቅዱስነታቸው እያንዳንዱን አማኝ "ቃል በቃል እንደሚያነጋግሩ ዓይነት ነው። አንባቢው ከእርሳቸው ጋር የጸሎት ሕይወትን እንዲመራ ያበረታቱታል። የግብጽን በረኃዎች፣ የአባቶችን ተጋድሎ በምናቡ

Name		Reported to(Project Mgt. Consult
Signature	Habtamu.M	Name
Date 08/09/21	08/05/2021	Signature
		Date

Scanned by CamScanner

ምስጋና

ይህንን መጽሐፍ ለንባብ እንዲበቃ ከጽንሰተ ሐሳቡ ልደቱ በምክር የተራዱኝን፣ በጸሎት ጉልበት የሆኑኝን አባቶች፣ እናቶች፣ ወንድሞችና እህቶች በሙሉ እግዚአብሔር ሰው አመሰግናለሁ።

ወንድሜ ዲን እሸቱ ሻሩ መጽሐፉን ኮምፒውተር እጅ መጨረሻ በማንበብ የነደለውን በመሙላት፣ የገበጠውን በማቅናት ላደረገልኝ እገዛ አመሰግናለሁ። ልዑል እግዚአብሔር የአገልግሎት ዕድሜ እንዲሰጠው እመኛለሁ። ወደፊትም በሙያቸው ሥራዎቼ ከጎኔ ሆኖ እገዛ እንደሚያደርግልኝ ተማምንበታለሁ።

ወንድሜ ጊታቸው በቀለ ፊደሉን በማረም ላደረገው ትብብር አመሰግናለሁ።

በመጨረሻም ውድ እንቴ መር ቀንጂት መልደማምት ቀን ከሊሊት በመትጋት፣ ጽሑፉን በመፃፍ ለጎትመት የተዘጋጀ እንዲሆን ላደረገችው እገዛ ልዑል እግዚአብሔር ውለታዋን ይክፈላት እላለሁ።

Scanned by CamScanner

ማውጫ

መግቢያ	ገጽ
የመጀመሪያ እንድ	1
የመጀመሪያ ሁለት	3
የመጀመሪያ ሦስት	28
የመጀመሪያ አራት	47
የመጀመሪያ አምስት	66
የመጀመሪያ ስድስት	83
የመጀመሪያ ሰባት	101
የመጀመሪያ ስምንት	119
የመጀመሪያ ዘጠኝ	143
የመጀመሪያ ዐሥር	184
የመጀመሪያ ዐሥራ አንድ	201
የመጀመሪያ ዐሥራ ሁለት	224
የመጀመሪያ ዐሥራ ሦስት	244
የመጀመሪያ ዐሥራ አራት	260
የመጀመሪያ ዐሥራ አምስት	290
የመጀመሪያ ዐሥራ ስድስት	309
የመጀመሪያ ዐሥራ ሰባት	326

Scanned by CamScanner

ኑፍሌ የወደደችህ

ብሔሪ ወትሩስ አቡነ ሺኖዳ ዛልላቢ

አንብስተማሩት

ትርጉም፡ ዲያቆን ታደለ ፈንታው

፩፱፻፰ ዓ.ም
አዲስ አበባ

Scanned by CamScanner



Scanned by CamScanner